በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ **8** የአብዮት አፀደ ህፃናትና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የ **2**ዐ**15** ዓ**.**ም**.** የ **6**ኛ ክፍል የህዳር ወር ፈተና

የጥያቄው ብዛት 6ዐ          የሚፈጀው ጊዜ 1፣15

ስም ------------------------------------------------------------ ክፍል --------------------- ቁጥር ----------------

<u>መመሪያ አንድ ከተራ ቁጥር **1-%** ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጪች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ /ምረጪ.</u>

<u>ምንባብ</u>

አሊ አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላው ነበር የሞቱት። በአብዛኞቹ የገጠር ልጆች ላይ እንደሚሰራው ሁሉ አሊም እረኝነት እጣው ፈንታው ሆነ። አንድ ቀን አሊ አጭር ግራር ሥር በሐሩር ጉልበት ተሸንፎ በራበው ሆዱ ተኝቶ ሳለ ከጆሮው ራቅ ወደጆሮው ቀረብ ራቅ ቀረብ የሚል ደስ የሚል ድምፅ ሰማ። ከሚያንጎላጅበት ቀና ሲል ድምፁ የሚመጣበትን አንድ ሽማግሌ ገበሬ የሚኖሩባትን አንዲት ደሳሳ ጐጆ ፊትለፊቱ አየ።

አንዴ ቆም ብሎ እየሰማ አንዴ ወደ እሳቸው እየተጠጋ ቆሞ እያዳመጠ ወደ ጎጆዋ እየተጠጋ እየቆመ እየተራመደ ፊታቸው ተገተረ። በቀኝ ክንዳቸው ስር የሸጎጡዋትን ጥቅርሻ የለበሰች ክራር እየገፋ ቀና ብለው በትናንሽ አየኖቻቸው አዩት። አሊም በፀሀይ ግለት ያብረቀረቀ የጠቆረ ፊቱን እያሸ ሽማግሌው እግር ስር ቁጭ አለ። የጸጸስ ቆብ መስሎ ከተራሮች መኸል የጎላ ተራራ ሆኖ ጠፍጣፋ ምድር ላይ የተተከለው ዳዲሞስ እየመሸ ሲሄድ ግዝፈቱና ግርማው መታየቱ ቀርቶ እየሟሟ ሲጠፋ የሽማግሌው ድምፅና የክራር ግርፍ ብቻ አካባቢውን ዋጠው ።

በአንድ ክንዱ ተደግፎ አቦ "ፋርጤን ፊታቸውንና ሁኔታቸውን በአይኑ እያቃኘ ሲያዳምጥ "መሸብህሒድ! በጎችህም እንዳይጣፋብህ" አሉትና በአንድ እጃቸው ራሱን ዳበሱት። አሊ በክራር ፍቅር ያኔ ነበር የተለከፈው።

ምንጭ ኤክስትሪም አማርኛ 5-8 ክፍል የተወሰደ

1. አሊ እናቱን በሞት ያጣው መቼ ነው?

   ሀ. በአንድ ዓመቱ    ለ. በሁለት ዓመቱ    ሐ. በሶስት ዓመቱ    መ. አምስት ዓመት ሳይሞላው

2.አሊ ከ<u>ሚያንጐላጅበት</u> ቀና እያለ ጽምፅ የሚመጣበትን ቦታ አጣራ። የተሰመረበት ቃል አሊ በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረ ይገልጻል?

   ሀ. በለቅሶ ላይ    ለ. በሳቅ ላይ    ሐ. በትዝታ ላይ    መ. በእንቅልፍ ላይ

3.በምንባቡ እንደኛው አንቀጽ ውስጥ " ...በሐሩር ጉልበት ተሸንፎ " የሚለው ሐረግ ትርጉም ከሚከተሉት አማራጫች መካከል የትኛው ነው

   ሀ. የስራጫና እስጎንብሶች    ለ. የፀሐይ ግለት አድክሞት    ሐ. ጐልበተኛ ደብድቦ ጥሎት    መ. ሰውዬው ተቆጥቶት

4.በሶስተኛው አንቀጽ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው የሚታዩት የስርዓተ ነጥብ አይነቶች ስንት ናቸው?

   ሀ. ሁለት    ለ. ሶስት    ሐ. አራት    መ. አምስት

5. ባለታሪኩ በክራር ስለመለከፋ የሚገልፀውን ሐሣብ የያዘው አንቀጽ ስንተኛው ነው

   ሀ. አንደኛው አንቀጽ    ለ. ሁለተኛው አነቀጽ    ሐ. ሶስተኛው አንቀጽ    መ. አራተኛው አንቀጽ

6.በአብዛኛው የገጠር ልጆች የሚሰሩት ሥራ ምንድን ነው

   ሀ. የዋሸንት ጨዋታ    ለ. እረኝነት    ሐ. ንግድ    መ. ሹፌር

7.የሸማግሌው መኖሪያ ምን አይነት ነበር?

ሀ. ደሳሳ ጎጆ ለ. የጎላ ተራራ ሐ. ከተራራው መሀል መ. ጠፍጣፋ ምድር ላይ

8.ሸማግሌው ክንዳቸው ስር የሸጉጡዋትን ጥቀርሻ የለበሰችው ምንድን ነበረች?

ሀ. ሹራብ ለ. ክራር ሐ. ዋሽንት መ. ልብስ

9" እየቃኙ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. እያመራ ለ. እየተቀመጠ ሐ. እየተመለከተ መ. እየደነሰ

%. የቀረበው ምንባብ ስንት አንቀጽ አለው?

ሀ. አንድ ለ. ሁለት ሐ. ሶስት መ. አራት

<u>መመሪያ ሁለት ከተራ ቁጥር %1-) ለቀረቡት ሰዋሰዋዊ የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያውን ፊደል ምረጥ /ጭ</u>

%1.ከሚከተሉት አማራጫች ውስጥ በፋቹ ልዩ የሆነው የቱ ነው

ሀ. ደከመ ለ. ተመፀወተ ሐ. ለመነ መ. ቀላወጣ

%2.ከሚከተሉት አማራጨች ውስጥ <u>የተፀውኦ ስም</u> የሆነው ምረጡ ።

ሀ. ሰለሞን ለ. ወንበር ሐ. ወረቀት መ. ወንድ

%3.ቀጥሎ ከቀረቡት መካከል የወል ስም የሆነውን መረጥ/ጭ

ሀ. ዳንኤል ለ. ራስዳሽን ሐ. ኬንያ መ. ቤት

%4.እመቤት ጉበዝ ተማሪ ናት። የአ/ነገሩ ባለቤት ----------- ነው።

ሀ. ተማሪ ለ. ጉበዝ ሐ. ናት መ. እመቤት

%5.አንድ አይነት የሆኑ ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት ስም /መጠሪያ ----------- ነው።

ሀ. የተፀኦ ስም ለ. የወል ስም ሐ. የጥቅልስም መ. የረቂቅ መጠሪ ስም

%6 ትርጉም የሌለው ብቻውን መቆም የማይችል ምዕላድ ------ ይባላል።

ሀ.ነፃ ምዕላድ ለ. ጥገኛ ምዕላድ ሐ. ግስ መ. ባለቤት

%7" እየሄደች" የሚለው ምዕላድ ተተንትኖ ሲጻፍ ---------- ይሆናል።

ሀ. እየ-ሔደች ለ. እ-ሔደ-ች ሐ. እየ-ሔደ-ች መ. እ-የ-ሄ-ደ-ች

%8 የአንቀጽ መሰረታዊ አካላት የምንላቸው የትኞቹ ናቸው

ሀ. ነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ ለ. ባለቤትና ተሳቢ ሐ. ኃይለቃልና መዘርዝር መ. የወልና የተደውኦ ስም

%9 ከሚከተሉት ስሞች መካከል እምር የሆነውን ስም ምረጡ

ሀ. ውሻ ለ. ሰው ሐ. በሬው መ. ደብተር

&.የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት ምንድን ነው

ሀ. ብዙ ቁጥርን ያመለክታሉ ለ. ባለንብረትነትን ያመለክታሉ ሐ.ጾታን ያመለክታሉ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

&1.ከሚከተሉት አማራጫች ውስጥ ባለንብረትነትን የሚገልጸው የትኛው ነው

ሀ. መፅሐፋችን ለ. መፅሐፎች ሐ. እነመፅሀፊ መ. መፅሀፍት

&2 ማርታ ግጥም አነበበች፡፡ የተሰበረበት ቃል ------------ የባላል፡፡

ሀ. የተጸውኦ ስም ለ. የወል ስም ሐ. ቅፅል መ. ተውሳከ ግስ

&3.አ/ነገሮች እርስ በርሳቸው ተገጣጥመው አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ ለመግለፅ የሚያገለግል አነስተኛ የድርሰት ክፍል ------ ይባላል፡፡

ሀ. አንቀጽ ለ. ድርሰት ሐ. አ/ነገር መ. ግጥም

&4 ከሚከተሉት አማራጨች ውስጥ ነፃ ምዕላድ የሆነውን ቃል ምረጡ

ሀ. እርሳስ ለ. አስደነገጠ ሐ. ወንበሩ መ. ቤቶች

&5 በፅሁፍ ያለን መልዕክት/ሀሳብ በአግባቡ እንዲረዱት ያደርጋል፡፡

ሀ. ስርዓተ ነጥብ ለ. የቃል ክፍሎች ሐ. አንቀጽ መ. ቢጋር

&6 የአንቀጽን ቅርፅ የሚወስንልን ምንድን ነው

ሀ. ግጥም ለ. ኃይለቃል ሐ. መዘርዝር መ. ቢጋር

&7" እሱ"እሷ &እነሱ" የሚሉት ተውላጠ ስሞች ስንተኛ መደብ ናቸው?

ሀ. አንደኛ መደብ ለ. ሁለተኛ መደብ ሐ. ሶስተኛ መደብ መ. መደብን አይገልጹም

&8 ከሚከተሉት አማራጫች ውስጥ በብዙ ቁጥር የተገለፀው የቱ ነው

ሀ. መርከብ ለ. በሬው ሐ. ወንበሮች መ. ልብስ

&9" ዛፎች" የሚለው ቃል በምን ጾታ ተገለጿል

ሀ. በተባዕታይ ለ. በተባዕታይና በአነስታይ ሐ. በአነስታይ መ. መልሱ የለም

'መስፍን ነጭ መኪና ገዛ። የተሰመረበት ቃል ምን ይባላል

ሀ. ባለቤት ለ. ቅፅል ሐ. ግስ መ. ስም

'1.መሀመድ ሻይ ጠጣ። በሚለው አ/ነገር መሀመድ የሚለውን ስም የሚተካው የተውላጠ ስም የቱ ነው

ሀ. እሳቸው ለ. እኔ ሐ. እናንተ መ. እሱ

'2.አይነት ገላጭን የሚያመለክት ምዕላጽ የያዘው የቱ ነው

ሀ. አሸዋማ ለ. ኢትዮጵያዊ ሐ.በጉ መ. ድመቲት

'3 ሰምሶም የክፍላችን አለቃ ነው። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው ---------- ነው ።

ሀ. ሀላፊ ለ. ሀይለኛ ሐ. አሳዛኝ መ. ትሁት

'4.ይዘት /አንድ ነጥብ ለምን ያገለግላል

ሀ. አሳጥሮ ለመጻፍ ለ. አጋኖ ለማቅረብ ሐ.ጥያቄ ለመጠየቅ መ. ተቃራኒ ሀሳብን ለመግለፅ

'5.ምዕላድ በስንት ይከፈላል

ሀ. በሁለት ለ. በሶስት ሐ. በአራት መ. በአምስት

'6." እንግዳ " ለሚለው ቃል ተቃራኒውን ምረጡ ።

ሀ. ዘመድ ለ. ወዳጅ ሐ. ቤተኛ መ. ዘመናዊ

'7.በሜዳው ላይ ነጭ ፍየል ይታያል። በአ/ነገሩ ውስጥ ያለው የስም ገላጭ -------- ነው።

ሀ. ነጭ ለ. በሜዳው ሐ. ላይ መ. ፍየል

'8." ከሰጠው " ይህ ቃል ቅጥያው በየት ቦታ ተቀጥሏል

ሀ. መነሻ ቅጥያ ብቻ ይዟል ለ. መድረሻ ቅጥያ ይዟል ሐ. መነሻና መድረሻ ቅጥያ መ. ምንም ቅጥያ አልያዝም

'9.እኔ ኳስ መጫወት እወዳለሁ። በሚለው አ/ነገር የተሰመረበት ቃል ----------- ነው።

ሀ. ግስ ለ. ቅፅል ሐ. ሰም መ. ተውላጠ ስም

(" ፍትሃዊ " በሚለው ቃል ላይ የተጨመረው ቅጥያ የቱ ነው

ሀ. -ዊ ለ. -ሃዊ ሐ. ፍት መ. ኣዊ

(1.የግጥም አንድ መስመር ምን ይባላል

ሀ. ሐረግ ለ. ስንኝ ሐ. ቤት መ. አንጓ

(2.ከሚከተሉት አማራ Ä ች ውስጥ ከግጥም ቃላት ውስጥ ይመደባል

ሀ. አንቀጽ ለ. ቤት መምቻ ሐ. አ/ነገር መ. ቅጥያ

(3.በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ትኩረት የሚደርጉ የስንኞች ስብስብ -------- ይባላል።

ሀ.ቤት ለ. ቤት መምቻ ሐ. አንጓ/አርኬ መ. ስንኝ

(4 ቃላዊ ግጥም ማለት የስነቃል ዘርፍ ሲሆን በ ------- ሲተላለፍ የመጣ ነው።

ሀ. በፅሁፍ ለ. በመፅሐፍ ሐ. በደብዳቤ መ. በቃል

(5 ቃላዊ ግጥም መቼ ይዜማል /ይገጠማል

ሀ. በሀዘን ጊዜ ለ. በበዓላት ጊዜ ሐ. በስራ ጊዜ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

(6.የቃላዊ ግጥም ደራሲ ማን ነው

ሀ. ማህበረሰቡ ለ. ዘሪሁን አስፋው ሐ. ሀዲስ አለማየሁ መ. በአሉ ግርማ

(7.ይችን ማጭዴን ሆዷን አሟታል&

እየቆረጠ ያጋድማታል ፡፡

ይህ ቃላት ግጥም በ --- ጊዜ ይዜማል።

ሀ.በአጨዳ ጊዜ ለ. በውቂያ ጊዜ ሐ. በቀረርቶ ጊዜ መ. በፋከራ ጊዜ

(8.እንጀራውን ጋገርሽ ከማን ጋር በላሽው&

ጠላውንስ ጠምቀሽ ከማን ጋር ጠጣሽው&

ደረት የሚመታ ጐረቤት ያጣሽው።

ይህ ቃላት ግጥም ለምን አይነት ሴት የተገጠመ ነው

ሀ. ደግ በመሆኗ ለቅሶዋ ለደመቀላት ሴት። ሐ. ንፋግ በመሆኗ ለቅሶዋ እንደነገሩ ለሆነላት ሴት።

ለ. ዘመድ አልባ ሆና አልቃሽ ላጣች ሴት። መ. ግጥሙ የሴትዮዋን ምንነት አይገልፅም።

(9 በተራ ቁጥር አርባ ስምንት ላይ የቀረበው ቃላዊ ግጥም ስንት ስንኞችን ይዟል

ሀ. ሶስት ለ. አራት ሐ. አምስት መ. ስድስት

).ሞፈሩ የብረት ቀንበሩም የብረት

ምድርን ያረሰበት ----። ግጥሙን ሊያሟላ የሚችል

መድረሻ ሀረግ ----- ነው።

ሀ. እህል ያስቀመጠበት    ለ. ሰው ያፈረሰበት    ሐ. እህል ያፈሰበት    መ. ያዘነበት ሰዓት

<u>*መመሪያ ሶስት ከተራ ቁጠር )1 እስከ )5 ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የያውን ቃል ምረጥ/ጭ*</u>

)1.አፀፋ

ሀ. ውሸት    ለ. መንገድ    ሐ. ምላሽ    መ. ንደት

)2.መቅሰም

ሀ. መማር    ለ. ለመውጣት    ሐ. ማየት    መ መታው

)3.ማጠራቀም

ሀ. መበታተን    ለ. ማከማቸት    ሐ. ማስፋፋት    መ. መስረቅ

)4.አመል

)3 አመል

ሀ. ዕራይ    ለ. ባህሪ    ሐ. ክፋ    መ. ሩህርህ

)5 ተስፋ

ሀ. ችሎታ    ለ. አጋጣሚ    ሐ. ምኞት    መ. ስልጠና

<u>*መመሪያ አራት ከተራ ቁጥር ) 6 እስከ * ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመምረጥ መልስ/ሽ*</u>

)6 ማግኘት

ሀ. ማጐልበት    ለ. መኖር    ሐ. ማፍራት    መ. ማጣት

)7.ባህላዊ

ሀ. የሚያምር ለ. ዘመናዊ ሐ. ታሪክ መ. ግዙፍ

)8.መብለጥ

ሀ. ማደግ ለ. ማነስ ሐ. መውጣት መ. መታየት

)9.በጋራ

ሀ. በአንድነት ለ. በህብረት ሐ. በግል መ. ብዙ

* . ምስጢር

ሀ. ድብቅ ለ. ውሸት ሐ. እውነት መ. ገሃድ

አዘጋጅ መ/ርት ባንቺ አፈወርቅ